

## ተባረኬ አህያ *

ሥጋሽን ለምግብ

ቆዳሽን ለገበያ

ቢዳርጉሽም ቻይኖች

እኔ ግን የማውቅሽ

ባደግሁበት መንደር፤

ከመጫን በስተቀር

ሳትገደይ ነበር።

ተባረኬ አህያ

አንች የድሃ ወዳጅ እኔ ልመርቅሽ፤

ተባረኬ ብየም ሃውልት ላቁምልሽ።

የሐገሪ ህዝቦች በቀልድ አትለፉት፣

የአህያን መበላት።

መሬቱን ቸርቸው ንብረትም ሲዘርፍ፤

ቸርቻሪው ገዥ ሲሆን

ፍርድ እንዲሰተካከል ማን፣ ማንንስ ይዝለፍ?

የሐገሪ ሕዝቦች እንደቀልድ አትዩት፤

ቻያናው ሲበዘብዝ አህያን በመብላት።

ሁሉም ተበዝብዞ አገር ሲሆን ባዶ

ይልቅስ አስቡ ምን እናርግ ብላችሁ፣

እምቤልታንም ንፉ ቀኑ ሳለላችሁ፤

ለዓለምም አሰሙ እምቢ እያላችሁ።

© ለምለም ፀጋው፤ በ ሳተናው ስለ አህያ በቻይና በተጻፈው ዜና የተነሳሳ ግጥም፣
አህያን ከመበላት ለማዳን ነው። April 6, 2017

<u>የፎተግራፍና የዜናው ምንጭ –</u>*http://www.satenaw.com/tplf-donkey-meat-skins-business-rattles-ethiopians/